ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshwegenie.org

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *መስከረም ፳፣ ፪ሺ ፲፮ ዓ.ም. (September 19, 2023)* *ቅጽ ፲ ቁጥር ፬*


# ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ) የዐማራ ህዝባዊ ኃይል ፋኖን የህልውና ትግል ይደግፋል። በአቶ እስክንድር ነጋ ቆራጥ አመራርም ይተማመናል።

ወያኔን በተረኝነት የተካው አረመኔው፣ ደፍጣጩና የዐማራን ህዝብ በአስቃቂ ሁኔታ እየጨረሰ የሚገኘው የአብይ አህመድ የብልፅግና አገዛዝ ኢትዮጵያን ለማፍረስና በኢትዮጵያ ፍርስራሽ "ታላቋን ኦሮሚያ" ለማዋለድ እየጣረ ነው። የኦሮሙማ የቅዠት ፓለቲካን እውን ለማድረግ የጠቅላይ ሚንስትር ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የኦሮሚያ ክልል እየተናበቡ፣ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ እየፈበረኩና እየነዙ፣ ታንኩንም ባንኩንም ተቆጣጥረው በዐማራ ህዝብ ላይ የጭካኔ በትራቸውን ለማሳረፍ እየሞከሩ ነው። አገዛዙ ሸኔ የሚባል ወንጀለኛ ገዳይ ቡድን፣ ትጥቅና ስንቁን አሟልቶና በጫካ አሰማርቶ የዐማራን ህዝብ ያለማቋረጥ ለ 5 ዓመት እንደሚያስፈጅ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ጉዳይ ነው።

አሁን ደግሞ በኮማንድ ፓስት ሰበብ ሀገር ይታደጋል የተባለ መከላከያ ሰራዊት ለብልጽግና አፋኝ ቡድን በማሰማራት የዐማራን ህዝብ ያለፍትህ በመግደልና ማጎሪያ ስፍራ አጉረው በተስቦና በኮሌራ በሽታ እየጨረሱት እንደሆነ የአደባባይ ሀቅ ነው። ሆኖም መካድና ሀሰት መናገር የማይታክተው የኦሮሙማው አገዛዝ እንደተለመደው የማጎሪያ ቦታ የለኝም በማለት ክዷል። በሚያሳፍር ሁኔታ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር ጭምር ኢትዮጵያ በሰብዓዊ መብት ጥሰት ቀዳሚዋ እንደሆነች ምስክርነት ሰጥቶበታል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር ባቀረበው ዘገባ አገዛዙ ሰላማዊ ሰዎችን በክልላቸው በነፃ እርምጃ በመረሸን፣ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የዐማራ ነገድ ተወላጆችን ከመላው ኢትዮጵያ ሰብስቦ በማጎሪያ ቦታ በማጎር እያሰቃየና በተስቦ በሽታ እየጨረሰ እንደሆነ አሳውቋል።

ወላድ በድባብ ትሂድና የዐማራ ህዝብ የህልውና ትግል የሚያደርጉና ራሳቸውን ሰውተው ትውልድ በነፃነት እንዲኖር የሚያደርጉ እጅግ ብዙ ጀግና ልጆች ተፈጥረዋል። ሆኖም በአለፉት 32 የመከራ ዐመታት በተለይም በአለፉት 5 አመታት ብዙ መስዋዕትነት ቢከፈልም የፓለቲካ አመራሩን የያዙት፣ አንድም ፀረ ዐማራ ኃይሎች ስለሚጠልፉት ወይም ዐማራም ቢሆኑ ስልጣን ላይ የሚንጠላጠሉት የብአዴን/አዴፓ ውላጅ፣ ለጥቅም የተሸጡ፣ ቆራጥነት የጎደላቸው፣ ስልጣን ፈላጊዎችና ባንዳዎች በመሆናቸው የዐማራ ህዝብ መሪ አልባ ሆኖ መከራው እንዲረዝም ተደርጓል።

አሁን ግን በበጎ ስነምግባሩ፣ በታማኝነቱና በፅናቱ የሚታወቀው እንዲሁም ስለ አገሩና ወገኑ ሲል በብዙ ፈተና ተፈትኖ እዚህ የደረሰው አቶ እስክንድር ነጋ የአመራሩን ኃላፊነት ወስዷል። የዐማራ ህዝባዊ ኃይል ፋኖ ትግል በዘረኛ የኦሮሞ ፓለቲከኞች ከታወጀበት የዘር ማጥፋት ለመዳን የሚከፈል የመሰዋትነት ትግል ነው። ፋኖ የአብይ አህመድን አገዛዝ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የሚዋደቅ የቁርጥ ቀን ልጆች ስብስብ ነው። በመሆኑ ፋኖን የዐማራ ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተስፋ ድጋፉን እየለገሰው ይገኛል። ነገር ግን በውጪ አገር ፋኖን ለመደገፍ ውክልና አለን የሚሉት ተበራክተዋል።

ከቀደመው ልምዳችን በመነሳት በውጪ አገር ድርጅት የሚበዛው በተለያዩ አሉታዊና አለኝታዊ ምክንያት ይኖሩታል። ከነዚህም ውስጥ በአላማም ሆነ በግብ ልዩነት ሳይኖር፣ ከነባሩ ድርጅት ጋር ባለመግባባት ለትግሉ መቀላጠፍ ከማሰብ በቅን ልቦና ወይም በማን አለብኝነት የሚቋቋም ድርጅት እንዳለ ሁሉ፣ እንደተለመደው በአዴፓ/ ብልፅግና ረዥም እጅ ፋኖን ለማዳከም ድርጅት ይመሰረታል፣ ተብሎ ይገመታል።

የፋኖ ተወካይ በመሆን ራሳቸውን ካስዋወቁት የፋኖ የድጋፍ ድርጅቶች ውስጥ

- በአቶ እስክንድር ነጋ አስተዋዋቂነት እውቅና የተሰጠው የአማራ ህዝባዊ ግንባር ፋኖ፣
- ፋኖ ለህልውናና ለፍትህ ስዲሞክራሲ፣
- አለም አቀፍ የፋኖ አስተባባሪ ኮሚቴ ይገኙበታል።

***ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ) ፋኖን ለመደገፍ በውጪ አገር የተለያዩ ድርጅቶች መቀፍቀፍ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል ብሎ ያምናል። ምክንያቱም የህይወት መስዋዕትነትን በሚያስከፍል የህልውና ትግል ላይ በእዝዛ ስም የፓለቲካ ትግል ማድረግ ትግልን እንደማዳከም ይቆጠራል።*** *ይኸውም ፋኖን ለመደገፍ በፓለቲካ እሳቤ ተነስቶ ታጋዩንና መስዋዕትነት የሚከፍለውን ፋኖ ከውጪ በሚላከው ገንዘብ በማደናገር የህልውና ትግሉን በመጥለፍ አገር ቤት ያለውን የፋኖ ትግል ንጥቂያ ማድረግ በትግሉ ላይ ውሀ እንደመቸለስ ይቆጠራል። በውጪ አገር ከቅን አሳቢ፣ አገር ወዳዶች በተሰበሰበ ገንዘብና እርዳታ ፋኖን መከፋፈል ብዙ ዋጋ ያስከፍላል። ከህዝብ በተሰበሰበ ገንዘብ ፅያፍ ተግባር የሚፈፅሙትንም የህልውና ትግሉ በጠላት ቁጥጥር ስር እንዲውል ከሚያደርጉት ለይቶ ማየት አይቻልምና የዐማራ ህዝብ አይታገሰውም።*

ፋኖ የዐማራ ህዝብ ድጋፍ ያስፈልገዋል ሲባል ህዝቡ በአንድ ልብ ተሰባስቦ መደረግ ያለበትን ሁሉ እንዲያደርግ ማገዝ፣ የገንዘቡም ፈሰስ በአንድ ቋት ገብቶ በነአቶ እስክንድር ነጋ በኩል እንዲደርስ ማድረግ ማለት ነው። በመሆኑም ***አገር ቤት ያለው የአቶ እስክንድር ነጋ አመራር በውጪ አገር ያለውንም የፋኖ ውክልና አደረጃጀት ኃላፊነት ወስዶ ከፀረ ዐማራ ኃይሎችና ከአዴፓ/ብልፅግና ደባ የፀዳና የህዝብ መሠረት ያለው ሆኖ እንዲወጣ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።*** *ስለዚህ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አገር ቤት ትግሉን ከሚመራው ከአቶ እስክንድር ነጋ አመራር፣ በውጪ አገር ፋኖን የመወከል አደረጃጀቱ በቅን ልቦና፣ በመከባበርና በመተሳሰብ ላይ የተመሠረተና ወጥነት ያለው ሆኖ እንዲቀጥል የማያዳግም መመሪያ መሥጠት ይጠበቅበታል ብሎ ያምናል።*

በዚሁ አጋጣሚ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)

- የአማራ ህዝብ የህልውና ትግል ያገባናል፣ ችግሩ በማያዳግም ሁኔታ መቀረፍ አለበት የሚል ዐማራ ሁሉ ትኩረቱን በውጪ ከሚቀፈቀፉ ድርጅቶች ላይ እንዲያደርግና የኃይል መሳሳት እንዳያስከትል አጥፊውን ቡድን በተገኘው መንገድ እንዲያወግዝ፣
- መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በዐማራ ህዝብ ላይ፣ በክልሉ በህግ ማስከበር ሥም የሚደረገውን በከባድ መሣሪያና በድሮን ጭምር የታገዘ ጭፍጨፋ፣ እንዲሁም የዐማራ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ በመላው ኢትዮጵያ በተለያየ የማጎሪያ ስፍራው ታጉረው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የዘር ፍጅት አግባብ አለመሆኑን ተረድቶ እንዲቃወም፣
- መከላከያ ሰራዊት ለብልጽግና ስልጣን የሚያደርገውን ጦርነት ባስቸኳይ አቁሞ ለህዝብ ውግንናውን እንዲያሳይና ከዐማራ ህዝብ ጎን እንዲቆም ጥሪውን ያቀርባል።

የዐማራ ህልውና ትግል ድል ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ዋስትና ነው!

አንድ አማራ፣ አንድ ፋኖ!